በየ3 ወሩ የሚወጣ የኤሌክትሮኒክስ ዜና መጽሄት

# የገንዘብ ሚኒስቴር ዜና መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 1 መጋቢት 2017 ዓ.ም



MoF Main Gate: A modern landmark with a sleek glass facade

## Ministry of Finance and World Bank Launched the Annual Joint Project Portfolio Review

The Ministry of Finance, in collaboration with the World Bank, has commenced a Joint Project Portfolio Review to review and enhance the implementation of ongoing projects and programs supported by the World Bank.

This review meeting, which is opened jointly by Minister of Finance H.E Mr. Ahmed Shide and the World Bank Division Director for Eritrea, Ethiopia South Sudan and Sudan, Ms. Maryam Salim, aims to evaluate the implementation quality and progress of ongoing projects across all sectors, identify any bottlenecks, and craft action plans for improved project efficiency and outcomes that align with Ethiopia's development goals

## መንግስት በየዓመቱ 4.5 ቢሊዮን ዶላር በማውጣት ከውጭ ሀገር የሚያስገባውን ነዳጅ ለህብረተሰቡበ ድጎማ እያቀረበ መሆኑ ተገለጸ



መንግስት በየዓመቱ 4.5 ቢሊዮን ዶላርበማውጣት ከውጭ ሀገር የሚያስገባውን ነዳጅ ለህብረተሰቡ በድጎማ እያቀረበ መሆኑ የገንዘብ ሚኒሰትር ክቡር አቶ አህመድ ሺዴ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አመልክተዋል፡፡ ስለዚህም ባለፉት ዓመታት ለነዳጅ ድጎማ ብቻ ከ267 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ ሲሆን አሁን ባለው የዓለም ዋጋ በኢትዮጵያ ይሸጥ ቢባል በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ጫና ለማቃለል በድጎማ እየቀረበ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

## የፌዴራልና የክልሎች የፋይናንስ፣ የገቢዎች፣ የፕላንና ልማት 29 ኛው የምክክር መድረክ ተካሄደ



የምክክር መድረኩ በዋናነት ተግባራዊ እየተደገ ባልው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በመንግስት ፋይናንስ አሰተዳደር ስርዓት፣ በሀገራዊ የልማት እቅድ እና በገቢ ዘርፍ በተሰሩ ስራዎች ላይ በማተኮር በጅማ ከተማ ተካሂዷል።

በምክክር መድረኩ ላይ የመከፍቻ ንግግር ያደረጉት የገንዘብ ሚንስትር ክቡር አቶ አሕመድ ሽዴ እንደገለጹት ኢትዮጵያ የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባራዊ በማድረግ ላይ መሆኗን አስታውሰው የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ላይ በመመስረት ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ሀገሪቱ ቅድሚያ የሰጠቻቸውን የልማት ፕሮግራሞች ፋይናንስ ለማድረግ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል ሲሉ ተናግረዋል፡



መንግስት የወጪ በጀትን በዋናነኛነት በሀገር ውስጥ ገቢ በመሸፈንና የበጀት ጉድለት ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ለኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን ለማስፈን እየሰራ ይገኛል ሲሉ ክቡር ሚኒስትሩ ገልጸው የተሟላ ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ውጤታማነት በማረጋገጥ ረገድ ከፌዴራል እስከ ታችኛው የመንግስት መዋቅር ድርስ ርብርብ ማደረግ ይጠበቅብናል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

በምክክር መድርኩ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያ ስራዎች ያመጡት ለውጦች ተገምግመው የተገኙት ውጤቶች አበረታች ቢሆኑም ለውጡን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባም ተመላክቷል፡፡

## የመስክ ምልከታው ብዙ የተማርንበትና በጋራ የሚፈቱጉድለቶችን የለየንብት ነው ክቡር አቶአህመድ ሽዴ



በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ከታህሣሥ 1 እስከ 7/2017 ዓ.ም ለመስክ ምልከታ ሲንቀሳቀሱ የሰነበቱት የገንዘብ ሚንስትር ክቡር አቶ አህመድ ሽዴ የመስክ ምልከታው ብዙ የተማርንበትና በጋራ ሊፈቱ የሚገባቸውን ጉደለቶች የለየንበት ነበር ሲሉ ገለጹ።

ክቡር ሚኒስትሩ ለተከታታይ ሰባት ቀናት በክልሉ የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች በመዘዋወር በልማት ስራዎች ላይ የመስክ ምልከታ አድረገው በመልከታ የተገኙ ነጥቦች ላይ ከክልሉ የበላይ አመራሮች ጋር ውይይት በማድረግ ለተሻለ አፈፃፀም ግብረመልስ ሰጥተዋል።

## የገንዘብ ሚኒስቴር የኢትዮጵያንየታክስህጎች የመተርጎምና የማደራጀት ስራውን አጠናቆ በድረ ገጹ ተደራሽ አደረገ




ሚኒስቴሩ የኢትዮጵያን የታክስ ህጎች ለመተርጎምና ለማደራጀት ሌክሲስ ኔክሲስ የህግ የበላይነት ተቋም (Lexis Nexis Rule of Law Foundation) ከተባለ ድርጅት ጋር ሲያከናውነው የነበረውን ፕሮጀክት በማጠናቀቅ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በሚኒስቴሩ የመስብሰቢያ አዳራሽ አስመርቋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር ዶ/ር እዮብ ተካልኝ በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ይህ ፕሮጀክት ሲጀመር ተደራሽነትን፣ ግልጽነት እና ቅልጥፍናን ማሻሻል በሚሉ ሶስት ዋና ዋና ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ እንደነበር አመልክተው እድገትና ልማቷን ለማፋጠንና የአለም የንግድ ድርጅት አባል ሀገር ለመሆን ለምታደርገው ጥረት ለአለም አቀፍ ኢንቨስተሮች ስለታክስ ህጎቿ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በድረ-ገጽ ተደራሽ መሆኗ ታላቅ ጠቀሜታ እንዳለው አስረድተዋል።




## The 57th Session of the Economic Commission for Africa Conference of Ministers of Finance, Planning, and Economic Development Concludes Successfully in Addis Ababa

**The 57th session of the Economic Commission for Africa (ECA) Conference of Ministers of Finance, Planning, and Economic Development (COM) successfully convened from 17–18 March 2025 at the ECA Headquarters in Addis Ababa, Ethiopia.**
**The conference brought together African finance, planning and trade ministers, central bank governors, regional institutions, development partners, as well as representatives from non-governmental organizations and the private sector. Nearly 400 participants attended the conference, including 30 high-level ministerial representatives from member states**

This year's conference was held under the theme "Advancing the Implementation of the Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area: Proposing Transformative Strategic Actions."

The opening ceremony featured a keynote address by H.E. Taye Atske Selassie (Ambassador), President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, who underscored the importance of accelerating the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) as a cornerstone of the continent's economic transformation.
Discussions during the conference centered on critical areas essential to the success of AfCFTA, including infrastructure development, cross-border instant payment systems, digital inclusion, and the role of special economic zones in fostering regional value chains. Delegates also explored strategies to enhance trade facilitation and industrialization across Africa.

To mark the occasion, the Federal Democratic Republic of Ethiopia hosted a state dinner on 17 March 2025 at the Skylight Hotel, extending a warm welcome to all participants. H.E. Ahmed Shide, Ethiopia's Minister of Finance, delivered welcoming remarks, emphasizing the conference's pivotal role in strengthening Africa's economic integration and cooperation.

# The 43rd Committee of Experts Meeting Opens in Addis Ababa to Shape Strategies for Advancing the African Continental Free Trade Area Implementation




The 43rd Committee of Experts meeting of the Conference of African Ministers of Finance, Planning, and Economic Development opened today in Addis Ababa, bringing together policymakers and experts to discuss strategies for advancing the implementation of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA).
The meeting focuses on the theme: "Advancing the Implementation of the Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area: Proposing Transformative Strategic Action."
H.E. Semereta Sewasew, Ethiopia's State Minister of Finance, in her opening remarks emphasized Africa's vision for intra-Africa trade development and shared prosperity through the African Continental Free Trade Area. The State Minister acknowledged significant challenges for the realization of the Continental Free Trade Area such as infrastructure gaps, fragmented policies, financing constraints, and security concerns.

To unlock the AfCFTA's potential, the speaker stressed the need for innovative solutions, greater collaboration, and investments in infrastructure development and energy. She highlighted the importance of inclusivity, particularly for women, youth, and small and medium-sized enterprises, urging collective action to ensure the AfCFTA becomes a transformative tool for tangible economic progress across the continent. Furthermore, the State Minister pointed out that AfCFTA's capacity to boost industrialization, job creation, and poverty reduction while addressing challenges such as financing constraints and policy fragmentation remain priority. The State Minister called for the need for in trade policy harmonization, and regional integration.

## ETHIOPIA AND THE WORLD BANK SIGNED A USD 700 MILLION FINANCING AGREEMENT TO STRENGTHEN THE FINANCIAL SECTOR

The Ministry of Finance and the World Bank signed a USD 700 million loan agreement to support the implementation of the Financial Sector Strengthening Project, which aims to enhance the stability and sustainability of Ethiopia's financial sector especially, the Commercial Bank of Ethiopia and the Development Bank of Ethiopia.

The agreement was signed by H.E. Ahmed Shide, Minister of Finance, representing the Government of Ethiopia, and Maryam Salim, Country Director for Ethiopia, Eritrea, Sudan, and South Sudan at the World Bank.

## H.E. Ahmed Shide and H.E. Amina J. Mohammed Discussed Accelerating SDGs in Ethiopia



H.E. Ahmed Shide, Minister of Finance of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, held a productive high-level meeting with H.E. Ms. Amina J. Mohammed, Deputy Secretary-General of the United Nations.

Both leaders underscored the critical role of collaboration between the Government of Ethiopia, the UN Country Team (UNCT) in Ethiopia, the United Nations Economic Commission for Africa (UNECA), and the UN Resident Coordinator's Office to align SDG initiatives with local development priorities.

# የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ውጤቶች

በማሻሻያው መሰረት የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ ሰነድ ማሻሻያ ተደርጎ የፌዴራል መንግስት ተጨማሪ በጀት ጸድቋል፣

የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ም/ቤ ጸድቋል

ነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ መድሐኒት፣ የምግብ ዘይት እና ልማታዊ ሴፍትኔት ድጎማ በጀት ተይዞ ክፍያ እየተፈጸመ ይገኛል፣

የመንግስት ሰራተኞች የኑሮ ውድነትን ማካካሻ የደመወዝ ማስተካከያ በጀት ተይዞ ክፍያ እየተፈጸመ ይገኛል፣

የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያው ኢኮኖሚው እንዲነቃቃ፣ የዋጋ ንረት እንዳይጨምር እና የኑሮ ውድነት እንዳይባባስ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋዕኦ አድርጓል፣

## ባለፉት ስድስት ወር በማክሮኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የተመዘገቡ የፊስካል ፖሊሲ አፈጻጸሞች






### ለዋጋ ማረጋጊያ የተወሰዱ እርምጃዎች

በበጀት አመቱ የመጀመሪያ ግማሽ አመት ለማዳበሪያ ግዥ ድጎማ ከተመደበው 100 ቢሊዮን ብር በጀት 16 ቢሊዮን ብር ተላልፏል። ለክልሎች የግብርና ግብዓት መግዣ ደግሞ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ213.2 ቢሊዮን ብር ዋስትና ተሰጥቷል። መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ከቀረጥና ታክስ ነጻ የተደረጉ ሲሆን በዚህም ምክንያት 2.2 ቢሊዮን ገቢ ሳይሰበሰብ ቀርቷል።

### ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተሰጠ የበጀት ድጋፍ

በ2017 በጀት ዓመት የተፈቀደ በጀት ብር 274.0 ቢሊዮን ሲሆን ለስድስት ወር የታቀደ ክፍያ ብር 115.9 ቢሊዮን ነው። በግማሽ አመቱ የተፈጸመ ክፍያ ብር 123.4 ቢሊዮን ሲሆን አፈጻጸሙም ከስድስት ወር ዕቅድ አንጻር 106.5 በመቶ፣ ከአመቱ ዕቅድ አንጻር ደግሞ 45 በመቶ ነው።



### የመንግስት ገቢና ወጪ አፈጻጸም

የመንግስት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የገቢ ዕቅድ ብር 600.3 ቢሊዮን ሲሆን በስድስት ወር ወስጥ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የገባ ብር 517.5 ቢሊዮን ነበር። የስድስት ወር አፈጻጸም ከግማሽ ዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸርጻር 86.2% ነው። የወጪ በጀት አፈጻጸምን በተመለከተም ለፌደራል መ/ቤቶች ክፍያ በ2017 በጀት ዓመት የተፈቀደ በጀት ብር 1,353.6 ቢሊዮን ሲሆን ለግማሽ አመቱ የታቀደ ብር 428.8 ቢሊዮን ነበር። በግማሽ አመቱ የተፈጸመ ክፍያ ብር 321.3 ቢሊዮን ሲሆን ከአመቱ ዕቅድ አንጻር 45 በመቶ ሲሆን ከግማሽ ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 75 በመቶ ነው።

### የመንግስት ገቢና ወጪ አፈጻጸም

**የመንግስት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የገቢ ዕቅድ ብር 600.3 ቢሊዮን ሲሆን በስድስት ወር ወስጥ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የገባ ብር 517.5 ቢሊዮን ነበር። የስድስት ወር አፈጻጸም ከግማሽ ዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸርጻር 86.2% ነው።**

**የወጪ በጀት አፈጻጸምን በተመለከተም ለፌደራል መ/ቤቶች ክፍያ በ2017 በጀት ዓመት የተፈቀደ በጀት ብር 1,353.6 ቢሊዮን ሲሆን ለግማሽ አመቱ የታቀደ ብር 428.8 ቢሊዮን ነበር። በግማሽ አመቱ የተፈጸመ ክፍያ ብር 321.3 ቢሊዮን ሲሆን ከአመቱ ዕቅድ አንጻር 45 በመቶ ሲሆን ከግማሽ ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 75 በመቶ ነው።**